# የሚያጠግብ እንጀራ

ሃያ ሰባት ዓመት ፣ አማራው ሲጠቃ
በግፍ ሲፈናቀል ፣ በጠፍ በጨረቃ
በትንሽ ትልቁ ፣ ሲበራይ ሲወቃ
ጨለማን ሲገፋ ፣ ሲያነባ በሲቃ ፣
ማነው የቆመለት ፣ ማን ሆነው ጠበቃ
ማንቀላፋት የለም ፣ ከመኝታህ ንቃ
ተደራጅተህ ታጠቅ ፣ የባለፈው ይብቃ ።

መቼ ሰከን አለ ፣ አልጋውም አልረጋ
ወገን በያለበት ፣ ያለቅሳል አልነጋ
ያለፈው ይበቃል ፣ እንዳትዘናጋ
ባትደራጅ ነው ፣ የከፈልከው ዋጋ ፣
ባራቱም ማዕዘን ፣ ሰይፉን ስትዘረጋ
መመከት ስትችል ፣ ታጥቀህ እንደዜጋ
ያኔ ያከብሩሃል ፣ እንኳን ልትወጋ ።

ይመጣል የከፋ ፣ ካለፈው የጠና
አልወጣችም ፀሃይ ፣ ገና አልነጋም ገና
እንዳለ ነው ዛሬም ፣ ጥቁሩ ዳመና
እንደቀድሞዎቹ ፣ ሁንና ቆፍጣና
ካሁን የተሻለ ፣ ጊዜ አይመጣምና ፣
አማራው ተደራጅ ፣ ስራ ጠንክርና
ነቃ ብለህ ተጓዝ ፣ አስተውለውና
እንዳያዘናጉህ ፣ በድምር ምርቃና
ሰርገኛ ሲመጣ ፣ ይቅር ደፋ ቀና ።

ለሀገር ያለህ ፍቅር ፣ ኢትዮጵያዊነትክን
በደም በአጥንትህ ፣ መስዋዕት መክፈልክን
በሉዐላዊነት ፣ ያለ ፅኑ እምነትክን
ጠላትም ወዳጅም ፣ ያውቀዋል ፅናትክን ፣
አማራው ተሰብሰብ ፣ አጎልብት እራስክን
ጋሻ ጦሩን አንሳ ፣ የናትና አባትክን
አንተ ተደራጅተህ ፣ ታደጋት እናትክን
ሁሉም ያውቃልና ፣ መዳረሻ ግብክን ።

አርባና ሃምሳ ዓመት ፣ መርዝ ሆኖ ስንቃቸው
ገነጣጥሎ ማፍረስ ፣ የሚያስብ ልባቸው
አንድነት ይበልጣል ፣ አይበጅም ያልካቸው
እንዳላሳደዱህ ፣ ከመንደር ቀዬአቸው ፣
አንተም ስትደራጅ ፣ ለምን አሰጋቸው?
ምን እንደሸረቡ ፣ እንደማናውቃቸው
ደርሶ አገር አፍቃሪ ፣ የቆረቆራቸው?
ዛሬም ሳይለወጥ ፣ ፅንፈኛ አቋማቸው
አንተን ለመተቸት ፣ ተከፈተ አፋቸው
እንዳያዘናጉህ ፣ ቦታም አትስጣቸው ።

አማራው ሲደራጅ ፣ አይናቸው የቀላ
ስኳራቸው ንሮ ፣ ደማቸው የፈላ
ያንድነት ሰባኪ ፣ የኢትዮጵያ ጥላ
መስለው አይታዩህ ፣ አትሁን ተላላ ፣
የሚዘባርቁ ፣ እንደጋፋ አንቡላ
የአረብ ተላላኪ ፣ የነጮች ቡችላ
እነ አደፍርስ ናቸው ፣ አይምሰሉህ ሌላ
ገሚሱ የቀን ጅብ ፣ ገሚሱ ነው ተኩላ ።

ችግር የወለደህ ፣ ከጭንቅ ከመከራ
ተደራጅተህ ታጠቅ ፣ ሰው ያሻውን ያውራ
ሴት ወጣት ገበሬ ፣ ምሁሩንም ጥራ
ይበጃል ያልከውን ፣ በማስተዋል ስራ
ተገንጣይ አስገንጣይ ፣ ውዥንብር ቢዘራ
እንደራሱ መስሎት ፣ ስራህ ለምንጠራ
ቢያሻው እንዳራዊት ፣ ይጩህ እንደቁራ ፣
በራስ መተማመን ፣ በማንነት ኩራ
ከተግባር ይማራል ፣ አይደለም ፉከራ
እናውቃለን እኛ ፣ የሚያጠግብ እንጀራ ።

ታዛቢው

August 16, 2018